ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ታኅሣሥ 17 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ሚዛን ክብደት ሊሰጣቸው የሚገባ ሀቆች

ለሕዝብ ትዝብትና ዕይታ ግልጽ ሆነው ያኲ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ተገቢ ቦታቸውም መስጠት ያስፈልጋል ። የግርግር ጫጫታ የሌለን ነገር ሀቅና ያለ አስመስሎ እንዳያደናግረን ማለት ነው ። ያለው ጠቅላይ ሚኒስቴር ለምሳሌ በሕዝብ አልተመረጠም--በተጭበረበረም ሆነ በነጻ። ስለዚህ ይህን ሰው ጠቅላይ ሚኒስቴሬ የሚለው ካለ ግለሰቡ በጠራራ ጸሃይ እየዋሸና እየሸነገለ ነው ማለት ነው ።ተወደድደ ተጠላ ሹሙ በቦታው የተሰየመው በሕዝብ ፍላጎትና ምርጫ ሳይሆን ሕዝብ ጠልት በሚለው ኢሕ አዴግ ተብዬ ጸረ ሕዝብ ስብስብ ነው ። ይህን ሀቅ መቀበልና ተገቢውን ግምገማና ደምዳሜ ማድረግ የሚጠበቅብን ሲሆን በስሜታዊ ይዘት ነጉደን ሰውየውን አምላክ ላከልን እስከማለት መድረስ ያስገምታል እንጂ አያስመሰግንም ። ስህተትም ነው--ሀገርን ትግልን የሚያበላሽ ስህተት ።

የሕዝብ ትግል የተሃሄደው የሲዳማውብ ጨፍጫፊ ሀይለማርያም ደሳለኝን በአዲሱ ሹም ለመተካት አልነበረም ። የተካሄደው ትግል የሕዝብ ሲሆን የፈሠውም ደም እንዲሁ የሕዝብ ነበር ። ደም አፍሳሹ ደግሞ ወያኔ ኢሕ አዴግ ሲሆን ሹሞቹ የዚሁ አረመኔ ቡድን አካልነ መሪዎችም ነበሩ ልልበርግጥ ዛሬ አዳዲስ ታሪክ እይቀረበ ሹሞቹ ለ 7ና 8 ዓመታት በህቡዕ ስንታገል ነበር ሊሉን ተነስተዋል። ሀሰትን ጥረቃ ነው ። የሕዝብን ትግል ሚና ክብደት ለማሳጣትና ድሉን ለመማት ። ለወያኔ ቀውስ ጠጥያቂ ሕዝብ እንጂ የዛሬ ሹሞች አይደለም ። የኦሮሞ ሕዝብ ታግሏል ግን ይህን ቂሮ የሚሉት ትግል አደናቃፊና ጠባብ ስብስባቸውን አይመለከትም ። በጎበዝ አለቃ ተደራጅቶ የታገለውም ሕዝብ ራሱን ፋኖ ብሎ ማዕከል መስርቶ እንዳልታገለ የምናውቀው ነው ። ስያሜ ሰጥቶ የሕዝብን ትግል የእናነ ነው ማለት ወይም ሳይታገሉና ሳያታግሉ ባለቤትነትን መውሰድ ጮሌ ፖለቲከኞች የተጠቀሙበት አደናጋሪ ስልት ነው ። የጎንደር ጎጃም ህዝብን ትግል የምመራው እነነኝ ሲል አንድ ቡድን ቀን ተሌት የሀሰት መግለጫ እያወጣ አንዲትም ጥይት ሳይተኩስ መሪ ነኝ ሲል አምጠና ታዝበናል ። ዛሬም ሹሞቹ ለዓመስት ታግለን ወያኒነ አዳከምነው ሲሉ የሕዝብን ሚና እየቀሙና በሀሰት ለራሳቸው ስም ሊሰጡ የተነሱ ነሆኑን አንስተውም ። በተስፋፋው ሀፍረት አልባ የሀሰት ዘመቻ አንድ ዕድሜ ይሉኝታን ያላባበሰው አንጅ ለምሳሌ የኢሕ አፓ መስራችና ሊቀመንበር ነኝ ብሎ በአደባባይ በተደጋጋሚ ሲዋሽም አድምጠናል ። የሹሞቹና የባዕድ መገናኛ ይህን ሀሰት በሰፊው ስርጭት የሰጠው ለእኩይ ጸረ ኢሕአፓ ዓላማው የሚጠቅመው መስሎት እንደሆነም መገመት ይቻላል ።ሀቁ ግን--በተጨባጭ እንደታየውና ሲሮጥ የሄደውን የከሀደት አንጃ አሳፍሮ እንደመለሰው--ያለ ኢሕ አፓ አንድና አንድ ብቻ ሲሆን በስሙ ሊነግዱ የቃጡትም የዚህ ድርጅት አባል ሳይሆኑ ዓመታት እንዳለፏቸው ለሁሉም ግልጽ ሊሆን ችሏል ። የሀሰት ዕድሜዋ ረጅም ቢመስልም በተጨባጭ ግን አጭር ነው። ወንጀልና ክህደት የፈጸሙትም፤ገራፊዎችና ግብረ ስየል ፈጻሚዎች በሰፈሩት ቁና እንዲሉ ደም ተፍተውና ስቃይን ተቀብለው ወደ መቃብራቸው ይጓዛሉ ። ትዕግስትና ቀጣይ ትግል--ሀቅ ያቸንፋል ።

በሹሞቹ የተወሰዱትን የተጠኑ ውሳኔዎች በማዳነቅና ውዳሴ በመስጠት--በዚህም የባዕድ ራዲዮና መገናኛዎች ከፍተኛ ሚና አላቸው - ያልሆነውን ሆነ እያሰኙ መሆናቸውንም መገንዘብ የግድ ነው ። ሴቶችን በብዛት ሾምን በማለት ስለ ሙብት አዲስ

መእራፍ የከፈቱ ቢያመስሉም በጽሬዛዳንትነት ሆነ በሌሎች ቦታዎች የሾሟቸው የወያኔ የመለስ ታማኝ ተከታዮች፤ካድሬዎች መሆናቸውን ሊሸፍኑ ቢሯሯጡም አልሆነላቸው ።የምርጫ ቦርድ ሀላፊ የህነችውም የቀድሞ ታቃዋሚግለሰብ ህጉ ባልተቀየረበት፤ኢሕአዴግ ከስልጣን ባልወረደበት፤አስመራጮች የአገዛዙ ሰዎች በሆኑበት የምትሰጠው ፋይዳ ብዙም እንደማይሆን ከወዲሁ መተንበይ የሚቻል ነው ። ሴት መሾምና ዴምክራሲ ግንኙነታቸው ቀጭን ለመሆኑ ደግሞ ከ50 በመቶ በላይ ሚኒስቴሮቹ ሴቶች የሆኑት የርዋንዳው ጭፍን አምባገነን ካጋሜ ምስክር ነው ። ዕምቡጥ አልባ ዳቦን መጋቢዎች ናቸውናም የይስሙላና አወናባጅ እርምጃዎችን በመውሰድ ዋናውን ጉዳይ ሸፍንፍን ያደርጋሉ ። ደርግ ከተራማጁ ትውልድ መፈክሮችን ቀምቶና ባዶ አድርጎ ያደረሰውን ጉዳት የሚያውቅ የሚረሳው አይደለም ። አፋዊ ለውጥና መና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሰጠውና--ረሃቡንም ቅንጣት ሳያስታግስለት--ዘመን አለፈ ። የማይጨበጥና የማይዳሰስ ነገርን ሲዳይ እያሉ ሕዝብን ሲያታልሉ ዓመታት አልፈዋል ። በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን ህገ መንግስት እንደነበር ብዙዎች የሚያስታውሱ አይመስልም ። የደርግም ህገ መንግስት ለእርቶ አደሩ ሕዝብ ሙብትን ያጎናጸፈ ተብሎ ነበር ። ለዚህም አጫፋሪዎች ነበሩ ። የወያኔንም የሚያዳንቁ እነ በረከት ስሞን ብቻ አይደለኡም ። አሜሪካ ራሷ የህግ የበላይነት መጣ ልትለን ሞክራ ነበር ። ዛሬ በሚሰራጬት በርካታ የሀሰት ዜናዎች ይምንረዳው ይህን የሹሞቹን ጉዞ ሊያሻሽሩ መሆኑን ነው ። በዓለም ደረጃ ውዳሲ ሹሙ እንዲጧጧፍ አሜሪካ ወዳጆችዋን ሰብስባ ከመምከሯ ባሻገር ከካሳ ከበደ መሰሎች በተጨማሪ ወደ ሰባት የሚደርሱ ልዩ አማካሪዎችን--በነሱ ስፒን ዶክተርስ የሚባሉትን--ልካለታለች ። አንዳንዴ የሹም የመለስለስ ሁኔታና ክብር የላመጠበቅ ድርጊት ግራ ቢያጋባ መካሪዎቹ የህገራችንን ሁኔታ እንደ ሀገሬው ደረጃ ያልተረዱት በመሆኑ ነው ። አጼ ዮሐናስን ንጉስ ስንላቸው ድንበር ልጠባ አሉ ብሎ በለሆሳስ የተቸው ሕዝባችን መሪህ ነኝ ያለው ግለሰብ በኢሳያስ ፊት ሲቅለሰለስ ሆነ የአረቡ መሪ ሹፌር ሲሆን ሊዋጥለት ባይችል አይደረደበትም ማለትም ትክክል ነው ።

የሕዝብ ዋናው ጥያቄና አሁን እየተከሰተ ካለው አደገኛ ሁኔታም ተከለካይ ሊሆንና ለሕዝብና ለሀገር አዲስ ምዕራፍን ከፋች ሊሆን የሚችለውን የሽግግር ሂደት ሹሞቹ ተው=ቃውመው የነበረውን ለመቀጠልና የራሳቸውን የግል ስልጣንና ጥቅም ማስቀደም እያደረሰ ያለው ጉዳት ግልጽ ነው ። ባዕዳኑ የሽግግር ሂደት ወደ ሕዝባዊ መንግስት ስለሚያመራና የሀገር ሉ ዓላዊነትንም እውን ስለሚያደርግ አይፈልጉትም ። ባእዳኑ ታሪክ እንዳሳየው ለሀገራቸውና ለአፍሪካ የቆሙ መሪዎችና መንግሥቶች እንዳይኖሩ ባላቸው ዓቅም ይጥራሉ ። ሉምሙባን የገደሉ ያስገደሉ፤ንክሩማህን የገለበጡ ያስገለበጡ አሜሪካና አጋሮቹዋ ናቸው ። ማንዴላን ሽብርተኛ ብላ ፈርጃ ከአፓርቴይድ ጎን የቆመቸውም አሜሪካ ነበረች። በመሆኑም ሕዝባዊ መንግሥት-ኢትዮጵያን የሚያስቀድም መንግሥት--እንዲኖር ስለማይፈልጉ የሽግግር ሂደትን ተጻረው ይቆማሉ ። ለዚህም ነው የሕዝብ ትግል አደናቅፈው ታዛዣቸውን ሹም ብለው የሰየሙብን ። በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረትና ራሳቸውም የሕዝብን ስልጣን ሊያስከብሩ የመጡ አይደሉምና ሹሞቹም የሽግግር ሂደትን ተቃውመው የነበረን ለማስቀጠል ሲወስኑ ራሳቸውንም ሀገራችንንም ወደ ባሰ ቀውስ መክተታቸው አልቀረም ። ባንድ በኩል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ፍጹም ስልጣኑ የተነካው ወያኔ በእሱ ብሶ የመገንጠልን ድንፋታ እስከማሰማት ደርሶ በየቦታውም የርስ በርስ ፍጅትን አባብሷል ። ይህን ከኦነግ ጋር የተቀናጀ ብጥብጥ ሲያካሄድም መጨረሻው ወደ ስልጣኑ ለመመለስ ወይም ከሕዝብ ቅጣት ለማምለጥ መሆኑ ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም ። በሌላ በኩል ደግሞ የሹሞቹ ለባዕድ ሎሌነትና የራሳቸውም የስልጣን ጥም የሽግግርን ሂደት ተቃርኖ ቀውሱን እያባባሰው ነው ። ያለውን ሁኔታ ለመቆጣጠር ችሎታም ፍላጎትም አቅምም የላቸውም ማለትም ይቻላል ። በየጊዜው ሊገሉኝ ነው፤ቅልበሳ መጣ ወዘተ በሚል የሹሙ ዋኡዋይታ መሰማቱ የሚያስገርም ሳይሆን የሚጠበቅ ነው

ማለትም እንችላለን ። የሽግግርን ሂደት መቃወማቸው ለሂደቱን ደካማ ጎን ማጠናከርና ለወያኔ ጥቃት መመቻቸት ነው ስንላቸው ስለማይሰሙ መጪውን ነውጥ ራሳቸው ላይ ራሳቸው ያመጡት ነው የምንለው ነው ።ለውጥ አምጪ ሕዝብ ሳይሆን እኛ ነን እስካሉ ጥቃቱንም ለመከላከል ራሳቸው ይወጡት በሚል ሕዝብ የሚወስን መሆኑንም መረዳት አለባቸው ። ኢትዮጵያን ለማዳን እንተባበር--ለስልጣናችን ሙቱልን--ሲሉ ሰሚ ያጣሉ እንጂ እንደ ባድሜ ጦርነት ጊዜ በስሜት የሚማገድላቸውን ዛሬ ሊያገኙም አይችሉም ። ያውም ደም የፈሠሰለትን መሬታችንን በዚህም በዚያም ለሻዕቢያም ለወያኔም ለሱዳንም እያስረከቡ ባሉበት ።

ለወያኔ ዋና ጠላቱ ሆኖ የተገኘው የሕዝብ ህብረትና ኢትዮጵያዊነት መሆኑ የሚዘነጋ መሆን የለበትም ። ይህን ሁኔታ ለምቀየር ወያኔ ሕዝብን እርስ በርስ በማበጣበጥ ህብረትን ሊያተን በመጣር ላይ ነው ። ኢትዮጵያዊነትንም ለማጥፋት ከከፈተው ዘመቻው አንዱና ዋነኛው ኢትዮጵያዊነትን ከብሄርተኝነት ጋር ማቃረን ነው ። በቅድሚያ ኢትዮጵያዊ ሳልሆን በብሄረሰቤ ልገለጽ የሚሉት ባለሜንጫዎች ዛሬ በሌሎችም ታጅበዋል ።ኢትዮጵያ የምንለውን እንደ ጸረ ብሄሮችና አንዱ ጠባብ ወንጀለኛ እንዳለውም እንደ ጨፍላቂ ሊፈርጁንም ተነስተዋል ። ኢትዮጵያዊነትን ከተዳከመ የወያኔ የምነትን ማጥበብ ይቀጥልና ሁሉም ተከፋፍሎ በየጎጡ የወያኔና የጠባቦች ሰለባ ይሆናል ። ሀገር ትከፋፈላላች፤ህልውናዋም አጠያያቂ ይሆናል ።ይህ የባዕዳንና የቆዩ የአካባቢ ጠላቶቻችን ምኞት ነው ። ኢትዮጵያዊነትን ማጠናከሩና ኢትዮጵያን የመጠብቁ ግዳጅ በአሁኑ ጊዜ ዋነኛው ግዳጃችን ሆኖ ይገኛል ። ይህን ለቅንጣትም መዘንጋት የለብንም እንላለን ።

ኢትዮጵያዊነት ይጠንክር !!

ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !

የሽግግር ሂደት ፍላጎታችን ይከበር !!